# የመጀመሪያ ልየታ ማሳወቂያ ቅጽ (ቴምፕሌት)

| ቀን፦ | የተማሪ ስም፦ |
|---|---|
| ዲስትሪክት፦ | ት/ቤት እና የክፍል ደረጃ፦ |

ውድ የ______________________________(Insert name of student)ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

ልጅዎ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ ሆኖ ተለይቷል። የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ ማለት፦ (1) የቤቱ ዋና ቋንቋ ከእንግሊዝኛ ውጪ የሆነ (2) በት/ቤት ውስጥ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመሳተፍ የቋንቋ ትምህርት እና ድጋፎችን የሚፈልግ ነው። የልጅዎን በእንግሊዝኛ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ እና የመጻፍ ብቃትን በተሻለ ለመረዳት የቋንቋ ዳሰሳ መጠይቅ እና የኦሃዮ የእንግሊዝኛ ቋኝቋ ብቃት ማጣሪያን (OELPS) ተጠቅመናል። እነሆ የልጅዎ ውጤቶች፦

*SCHOOL INSERTS OR ATTACHES OELPS INDIVIDUAL STUDENT REPORT (ISR)*

እንደ እንግሊዝኛ ተማሪ ልጅዎ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ትምህርታዊ ፕሮግራማችን አማካኝነት ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ነው። ፕሮግራሙ የልጅዎን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ልማትን ለመደገፍ እና በትምህርቶች እና በት/ቤት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ትርጉም ባለው መልኩ መሳተፍ መቻላቸውን ለማረጋገጥ ያግዛል። ይህ ደብዳቤ የልጅዎን የእንግሊዝኛ ችሎታ ደረጃን እና ልጅዎ በት/ቤት ውስጥ በተሟላ ሁኔታ መሳተፍ እንዲችል ለማገዝ የሚገኘውን ፕሮግራም ያብራራልዎታል።

የፕሮግራሞቹ ዓላማዎች የሌሎች ቋንቋዎች ተናጋሪ ተማሪዎችን በእንግሊዝኛ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ እና የመጻፍ ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ ለመርዳት ነው። ልጆችዎ በትምህርታቸው እድገትን ለማሳየት የሚያስፈልጋቸውን የቋንቋ ብቃትን እንዲያመጡ ለማገዝ ያሉት የዲስትሪክቱ ፕሮግራሞች የሚከተሉት ናቸው፦

*ት/ቤቱ ከዚህ በታች ያሉ ፕሮግራሞችን ወይም አሠራሮችን እንደአስፈላጊነቱ ሊያሻሽል ይችላል*

1. የእንግሊዝኛ-ብቻ ድጋፍ የትምህርት ፕሮግራም
2. የሁለት ቋንቋ ድጋፍ የትምህርት ፕሮግራም
3. ጥምር ቋንቋ (dual language) ፕሮግራም
4. የእንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ድጋፍ የተካተተባቸው የዋና ትምህርት ትምህርቶች
5. የአዲስ ገቢዎች ፕሮግራም
6. ለእንግሊዝኛ ተማሪዎች-ብቻ የሆነ ዋና ትምህርቶችን በቀላል እንግሊዝኛ የማስተማሪያ (Sheltered ትምህርት) ፕሮግራም
7. የተደራጀ ወይም ባለሁለት-መንገድ የንክረት (immersion) ፕሮግራም
8. ማማከር፣ ክትትል እና ትምህርታዊ ድጋፍ
9. ሌሎች፦

እያንዳንዱ ፕሮግራም በዚህ ደብዳቤ መጨረሻ ላይ በሙዳየ-ቃላት ውስጥ ተብራርተዋል።

ፕሮግራሙ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎቶችን ከማሳደግ በተጨማሪ ልጆችዎ ከክፍል ክፍል ለመዛወር እና ለምረቃ በየእድሜ ድረጃቸው የሚመጥኑ የትምህርት ውጤታማነት መስፈርቶችን ማሟላት እንዲችሉ ይረዳል።
ተማሪዎች በአጠቃላይ የብቃት ደረጃ ላይ ካልደረሱ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች በመባል ተመድበው ይቆያሉ። ይህም የሚወሰነው በየዓመቱ በስፕሪንግ በሚሰጠውበኦሃዮ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ምዘና (OELPA) ነው። የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች አጠቃላይ የብቃት ደረጃን የሚያሳዩት በአራቱም የፈተና ክፍሎች በእያንዳንዳቸው (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መጻፍ) 4 ወይም 5 ነጥብ ሲያገኙ ነው።

አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በ*INSERT PROGRAM RATE* ዓመት ውስጥ በእንግሊዝኛ ብቁ ሆነው ከፕሮግራማችን ይወጣሉ። ከፕሮግራም ሲወጡ ልጆችዎ ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸውና እንደማያስፈልጋቸው ለመወሰን ለሁለት ዓመት ያህል የአፈጻጸም ክትትል ይደረግላቸዋል

በ*INSERT SCHOOL YEAR*ዓመት ውስጥ *INSERT ADJUSTED 4-YEAR GRADUATION RATE* በመቶው የሚሆኑ የNAME OF SCHOOL ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በ4 ዓመት ተመርቀዋል እና *INSERT ADJUSTED 5-YEAR GRADUATION RATE* በመቶው የሆኑ ተማሪዎች በተጨማሪ አንድ ዓመት ውስጥ ተመርቀዋል።

ልጅዎ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ልማት ፕሮግራም እንዲሳተፍ አጥብቀን እናበረታታለን። ስለፕሮግራሙ ጥቅሞች የበለጠ እንዲረዱ ጋብዘንዎታል።

የልጅዎን የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት እና የትምህርት ውጤቶችን በተመለከተ ለመነጋገር እባክዎ ይደውሉልን ወይም ይጎብኙን።

*INSERT CONTACT NAME*
*INSERT CONTACT PHONE NUMBER*
*INSERT CONTACT EMAIL ADDRESS*

ት/ቤታችን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ሁሉ የማገልገል ግዴታ ቢኖርበትም እርስዎ ልጅዎ ከእንግሊዝኛ ትምህርት ፕሮግራም ወይም በፕሮግራሙ ውስጥ ከተወሰኑ አገልግሎቶቹ እንዲወጣ የማድረግ መብት አለዎ። ልጅዎን ከት/ቤቱ የእንግሊዝኛ ትምህርት ፕሮግራም ወይም ከተወሰኑት ፕሮግራሞቹ ውስጥ ቢያስወጡም የልጅዎ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪነት አቋማቸው እንደተጠበቀ ይሆናል። ት/ቤቱ በ1964ቱ የሰብዓዊ መብቶች አዋጅ አንቀጽ VI እና በ1974ቱ የፍትሃዊ ትምህርት እድል አዋጅ መሠረት ለእንግሊዝኛ ተማሪዎች የትምህርት ፕሮግራሞች አዎንታዊ እምጃዎችን እንዲወስድ ይገደዳል ((20 U.S.C. sections 1703[f], 6312[e][3][A][viii])።

☐ ይህን መረጃ ተረድቼ ልጄ በእንግሊዝኛ ቋንቋ አገልግሎቶች እንዲሳተፍ ተስማምቻለሁ።

☐ ይህን መረጃ ተረድቻለሁ። ግን ልጄ ከዚህ በላይ ባሉት ፕሮግራሞች ውስጥ እንዳይሳተፍ/እንዳትሳተፍ ስለማድረግ የዲስትሪክት ሠራተኛን ማነጋገር እፈልጋለሁ።

☐ ቋንቋውን አልተረዳሁትምና ይህ መረጃ እንዲገባኝ ተጨማሪ የቋንቋ ድጋፍ እና ማብራሪያ እፈልጋለሁ።

____________________________________________________
(በግልጽ የተጻፈ የወላጅ/አሳዳጊ ስም)

____________________________________________________
(የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ) ቀን (ወር/ቀን/ዓመት)

# የቀጠለ የእንግሊዝኛ ተማሪ/ልየታ ማሳወቂያ ቅጽ (ቴምፕሌት)

ውድ የ_______________________________(Insert name of student)ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

| **ቀን፦** | **የተማሪ ስም፦** |
|---|---|
| **ዲስትሪክት፦** | **ት/ቤት እና የክፍል ደረጃ፦** |

በየዓመቱ ልጅዎን እንድንመዝን/እንድንፈትን እና የልጅዎን የእንግሊዝኛ ብቃት ደረጃ እንድናሳውቅዎ እንገደዳለን። በኦሃዮ የእንግሊዝኛ፡ቋንቋ ብቃት ምዘና/ፈተና (OELPA) ውጤቶች መሠረት ልጅዎ የእንግሊዝኛ ተማሪ ተብሎ እንደተለየ ይቀጥላል። እነሆ የልጅዎ ውጤቶች፦

*INSERT OR ATTACH OELPA INDIVIDUAL STUDENT REPORT*

እንደ እንግሊዝኛ ተማሪ ልጅዎ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ትምህርታዊ ፕሮግራማችን አማካኝነት ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ነው። ፕሮግራሙ የልጅዎን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ልማትን ለመደገፍ እና በትምህርቶች እና በት/ቤት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ትርጉም ባለው መልኩ መሳተፍ መቻላቸውን ለማረጋገጥ ያግዛል። ይህ ደብዳቤ የልጅዎን የእንግሊዝኛ ችሎታ ደረጃን እና ልጅዎ በት/ቤት ውስጥ በተሟላ ሁኔታ መሳተፍ እንዲችል ለማገዝ የሚገኘውን ፕሮግራም ያብራራልዎታል።

የፕሮግራሞቹ ዓላማዎች የሌሎች ቋንቋዎች ተናጋሪ ተማሪዎችን በእንግሊዝኛ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ እና የመጻፍ ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ ለመርዳት ነው። ልጆችዎ በትምህርታቸው እድገትን ለማሳየት የሚያስፈልጋቸውን የቋንቋ ብቃትን እንዲያመጡ ለማገዝ ያሉት የዲስትሪክቱ ፕሮግራሞች የሚከተሉት ናቸው፦

*MODIFY LIST OF PROGRAMS OR APPROACHES BELOW AS NEEDED*

- የእንግሊዝኛ-ብቻ ድጋፍ የትምህርት ፕሮግራም
- የሁለት ቋንቋ ድጋፍ የትምህርት ፕሮግራም
- ጥምር ቋንቋ (dual language) ፕሮግራም
- የእንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ድጋፍ የተካተተባቸው የዋና ትምህርት ትምህርቶች
- የአዲስ ገቢዎች ፕሮግራም
- ለእንግሊዝኛ ተማሪዎች-ብቻ የሆነ ዋና ትምህርቶችን በቀላል እንግሊዝኛ የማስተማሪያ (Sheltered ትምህርት) ፕሮግራም
- የተደራጀ ወይም ባለሁለት-መንገድ የንክረት (immersion) ፕሮግራም
- ማማከር፣ ክትትል እና ትምህርታዊ ድጋፍ
- ሌሎች፦

እያንዳንዱ ፕሮግራም በዚህ ደብዳቤ መጨረሻ ላይ በሙዳየ-ቃላት ውስጥ ተብራርተዋል።

**ፕሮግራሙ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎቶችን ከማሳደግ በተጨማሪ ልጆችዎ ከክፍል ክፍል ለመዛወር እና ለምረቃ በየእድሜ ድረጃቸው የሚመጥኑ የትምህርት ውጤታማነት መስፈርቶችን ማሟላት እንዲችሉ ይረዳል።**

ተማሪዎች በአጠቃላይ የብቃት ደረጃ ላይ ካልደረሱ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችበመባል ተመድበው ይቆያሉ። ይህም የሚወሰነው በየዓመቱ በስፕሪንግ በሚሰጠው በኦሃዮ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ምዘና (OELPA) ነው። የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች አጠቃላይ የብቃት ደረጃን የሚያሳዩት በአራቱም የፈተና ክፍሎች በእያንዳንዳቸው (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መጻፍ) 4 ወይም 5 ነጥብ ሲያገኙ ነው።

አብዛኞቹ ተማሪዎች በ*INSERT PROGRAM RATE* ዓመት ውስጥ በእንግሊዝኛ ብቁ ሆነው ከፕሮግራማችን ይወጣሉ። ከፕሮግራም ሲወጡ ልጆችዎ ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸውና እንደማያስፈልጋቸው ለመወሰን ለሁለት ዓመት ያህል የአፈጻጸም ክትትል ይደረግላቸዋል።

በ*INSERT SCHOOL YEAR*ዓመት ውስጥ *INSERT ADJUSTED 4-YEAR GRADUATION RATE* በመቶው የሚሆኑ የ*NAME OF SCHOOL* ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በ4 ዓመት ተመርቀዋል እና *INSERT ADJUSTED 5-YEAR GRADUATION RATE* በመቶው የሆኑ ተማሪዎች በተጨማሪ አንድ ዓመት ውስጥ ተመርቀዋል።

ልጅዎ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ልማት ፕሮግራም እንዲሳተፍ አጥብቀን እናበረታታለን። ስለፕሮግራሙ ጥቅሞች የበለጠ እንዲረዱ ጋብዘንዎታል።

የልጅዎን የእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት እና የትምህርት ውጤቶችን በተመለከተ ለመነጋገር እባክዎ ይደውሉልን ወይም ይጎብኙን።

*INSERT CONTACT NAME*
*INSERT CONTACT PHONE NUMBER*
*INSERT CONTACT EMAIL ADDRESS*

ት/ቤታችን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ሁሉ የማገልገል ግዴታ ቢኖርበትም እርስዎ ልጅዎ ከእንግሊዝኛ ትምህርት ፕሮግራም ወይም በፕሮግራሙ ውስጥ ከተወሰኑ አገልግሎቶቹ እንዲወጣ የማድረግ መብት አለዎ። ልጅዎን ከት/ቤቱ የእንግሊዝኛ ትምህርት ፕሮግራም ወይም ከተወሰኑት ፕሮግራሞቹ ውስጥ ቢያስወጡም የልጅዎ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪነት አቋማቸው እንደተጠበቀ ይሆናል። ት/ቤቱ በ1964ቱ የሰብዓዊ መብቶች አዋጅ አንቀጽ VI እና በ1974ቱ የፍትሃዊ ትምህርት እድል አዋጅ መሠረት ለእንግሊዝኛ ተማሪዎች የትምህርት ፕሮግራሞች አዎንታዊ እምጃዎችን እንዲወስድ ይገደዳል ((20 U.S.C. sections 1703[f], 6312[e][3][A][viii])።

☐ ይህን መረጃ ተረድቼ ልጄ በእንግሊዝኛ ቋንቋ አገልግሎቶች እንዲሳተፍ ተስማምቻለሁ።

☐ ይህን መረጃ ተረድቻለሁ። ግን ልጄ ከዚህ በላይ ባሉት ፕሮግራሞች ውስጥ እንዳይሳተፍ/እንዳትሳተፍ ስለማድረግ የዲስትሪክት ሠራተኛን ማነጋገር እፈልጋለሁ።

☐ ቋንቋውን አልተረዳሁትምና ይህ መረጃ እንዲገባኝ ተጨማሪ የቋንቋ ድጋፍ እና ማብራሪያ እፈልጋለሁ።

__________________________________________________________

(በግልጽ የተጻፈ የወላጅ/አሳዳጊ ስም)

__________________________________________________________

(የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ) ቀን (ወር/ቀን/ዓመት)

# የቋንቋ ልማት ፕሮግራሞች መግለጫ

**የእንግሊዝኛ-ብቻ ድጋፍ የትምህርት ፕሮግራም፦** የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የአፍ መፍቻ ቋንቋን የማያካት የየዕለት ትምህርት ውስጥ ልዩ የቋንቋ ፍላጎቶችን ለማሟላት የተነደፈ ፕሮግራም። በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የሚሰጡት አማራጭ ትምህርቶች ምሳሌዎች እንግሊዝኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ (ESL) ትምህርቶች፣ ከክፍል ለይቶ ወስዶ የማስጠናት ክፍለጊዜዎች፣ ለይቶ ወስዶ ዋና ትምህርቶችን ማስተማር (ለምሳሌ ለእንግሊዝኛ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ደረጃ እንዲመጥን የተደረገ የሒሳብ ትምህርት) እና በዋናው መማሪያ ክፍል ውስጥ በESL ባለሞያ የሚደረጉ ድጋፎች (አካትቶት) ናቸው። **(235023)**

**የተደራጀ እንግሊዝኛ ወይም የESL ፕሮግራም፦** የዚህ ፕሮግራም ግብ የእንግሊዝኛ ተማሪዎች በእንግሊዝኛ-ብቻ ትምህርት በሚሰጥባቸው መማሪያ ክፍሎች ውስጥ ስኬታማ እንዲሆኑ ለማስቻል የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርትን ማስተማር ነው። መምህራን በሁለት ቋንቋዎች የተማሩ ወይም እንግሊዝኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የማስተማር ማስረጃ እና/ወይም ስልጠናው ያላቸው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ፍላጎቶች ለማሟላት ልዩ የሆነ ስልጠና ያላቸው ናቸው። የማስተማሪያ ቋንቋው እንግሊዝኛ **(235023)**

**የESL ድጋፍ የተካተተባቸው ዋና ትምህርቶች፦** እነዚህ የቋንቋ ድጋፎች ትምህርቶችን በእንግሊዝኛ ለማስተማር በልዩ ሁኔታ የተቀረጹ (SDAIE) ለእንግሊዝኛ ተማሪዎች-ብቻ የሆነ የዋና ትምህርት መማሪያ ክፍል ትምህርት ምልከታ ፕሮቶኮል (SIOP) ተብለው ሊታወቁ ይችላሉ። የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን፣ የትምህርት ተግባሮች እና የክፍል ውስጥ ቴክኒኮችን ከዋና ትምህርት መስኮች በመጠቀም ቋንቋን፣ ይዘትን፣ ዕውቀትን እና የጥናት ክህሎቶችን ለማዳበር በሁሉም አስተማሪዎች ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው። የማስተማሪያ ቋንቋው እንግሊዝኛ **(235019)**

**ለእንግሊዝኛ ተማሪዎች-ብቻ የሆነ ዋና ትምህርቶችን በቀላል እንግሊዝኛ የማስተማሪያ (Sheltered ትምህርት) ፕሮግራም የእንግሊዝኛ መማር ማስተማር፦** የዋና ትምህርቶችን ይዘት በእንግሊዝኛ ሲሰጥ ለእንግሊዝኛ ተማሪዎች ተደራሽ የማድረጊያ የመማር ማስተማር ዘዴ። በዚህ ለእንግሊዝኛ ተማሪዎች-ብቻ በሆነ የመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን የሒሳብ፣ የሳይንስ፣ የሶሻል ስተዲስ እና የሌሎች ትምህርቶችን ጽንሰ-ሀሳቦችን ለማስተማር የአካላዊ እንቅስቃሴዎችን፣ ምስላዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን እና አካባቢውን ይጠቀማሉ። **(235019)**

**የሁለት ቋንቋ ድጋፍ የትምህርት ፕሮግራም፦** የተወሰኑት ትምህርቶች በተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚሰጡበት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ልዩ የቋንቋ ፍላጎቶችን ለማሟላት የተቀረጸ ፕሮግራም። በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የሚሰጡ የመማር-ማስተማር አማራጭ ምሳሌዎች በሁለት ቋንቋዎች የማስተማር ፈቃድ ወይም ማረጋገጫ ባለው አስተማሪ (ለምሳሌ ሒሳብ በእንግሊዝኛ እና በስፓኒሽኛ) የሚሰጥባቸው የሁለት ቋንቋ ማስተማር ወይም ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ በሆነ ረዳት አስተማሪ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ማብራሪያ የሚሰጥባቸው ትምህርቶች ናቸው። በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በቀኑ የተወሰነ ክፍል ውስጥ በእንግሊዝኛ-ብቻ በሚሰጡ ትምህርቶች (ለምሳሌ የESL ትምህርቶች) ውስጥ ሊሳተፉም ይችላሉ። </b2><b3>(235025)</b3>

**ጥምር ቋንቋ (dual language) ፕሮግራም፦** ባለሁለት-መንገድ ንክረት (immersion) እየተባለም በሚታወቀው በዚህ ፕሮግራም ውስጥ እንግሊዝኛ ተማሪ የሆኑ እና እንግሊዝኛ ተማሪ ያልሆኑ ተማሪዎች ትምህርትን በእንግሊዝኛ እና እንግሊዝኛ ባልሆነ ቋንቋ ይማራሉ። ጥምር ቋንቋ ፕሮግራም ከፍተኛ የትምህርት ውጤታማነት፣ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ቋንቋ ብቃትን እና የተሻጋሪ-ባህል መረዳትን እንደግቦቹ በመያዝ ቋንቋን እና የዋና ትምህርቶችን አዋህዶ እንግሊዝኛ የአፍ መፍቻቸው ለሆነ እና የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሌላ ለሆነ ተማሪዎች ይሰጣል። **(235017)**

**የአዲስ ገቢዎች፦** የአዲስ ገቢዎች ፕሮግራሞች አዲስ የሚመጡ ስደተኞችን የትምህርት እና የባህል ፍላጎቶችን ለማሟላት የተቀረጹ የተናጥል በአንጻራዊነት ራሳቸውን የቻሉ ሥርዓቶች ናቸው። ብዙውን ጊዜ ተማሪዎች እነዚህ ፕሮግራሞች የሚቀላቀሉት መደበኛ (ለምሳሌ እንደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ልማት ፕሮግራሞች ወይም ከESL ድጋፍ ጋር የተቀናጁ የዋና ትምህርት መማሪያ ክፍሎች ያሉ) ፕሮግራሞችን ከመቀላቀላቸው በፊት የሚከታተሏቸው ናቸው። **(235021)**

**ሌሎች ፕሮግራሞች**

ባሉት ሌሎች የእንግሊዝኛ ተማሪዎች ፕሮግራም ደንቦች (ኮዶች) ያልተሸፈኑ ሌሎች የእንግሊዝኛ ተማሪ ፕሮግራሞች። ማማከርን፣ ክትትልን እና ትምህርታዊ ድጋፍን ያካትታሉ፦ የእንግሊዝኛ ተማሪዎችን እንደህዝብ፣ እንደግለሰቦች እና እንደቋንቋ ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ለመደገፍ የሚያስችሉ መረጃዎችን እና ግብዓቶችን ለማግኘት በመምህራን እና በልዩ ባለሙያዎች መካከል የተለዩ መስተጋብሮች ላይ የተደረገ የጋራ ስምምነት። የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ደረጃዎች በሥርዓተ ትምህርቱ በሞላ የሚተገበሩ ናቸው። የእንግሊዝኛ ተማሪ (EL) ፕሮግራሞች ተፈላጊ መስፈርት። **(235099)**

**ማጣቀሻዎ**

*የዩ.ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት። የቋንቋ ማስተማር ትምህርታዊ ፕሮግራሞች (LIEP)፦ የመሠረታዊ ሥነ-ጽሑፍ ግምገማ*

*የተዘረዘሩ ደንቦች (Codes) ወደ ODE EMIS Manual 2.9 ይመራሉ*

# የእንግሊዝኛ ቋንቋ ፕሮግራም አለመቀበልን የማሳወቂያ ቅጽ (ቴምፕሌት)

| | |
|---|---|
| **ቀን፡-** | **የተማሪ ስም፡-** |
| **ት/ቤት፡-** | **ት/ቤት ዲስትሪክት እና የክፍል ደረጃ፡-** |

ውድ የ________________________________(Insert name of student)ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

ለልጅዎ የቀረበውን የቋንቋ መማር-ማስተማር ትምህርታዊ ፕሮግራም ላለመቀበል እንደፈለጉ ተረድተናል። የእንግሊዝኛ ቋንቋ ፕሮግራሞች የልጅዎን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ለማሳደግ እንዲሁም በክፍል-ደረጃው ትምህርቶች ውስጥ መሳተፍ እንዲችል ለማገዝ በተለይ የተነደፉ ናቸው። ሆኖም ግን በንግግራችን ጊዜ እንዳስረዳንዎ ለልጅዎ የቀረበውን ፕሮግራም ያለመቀበል ወይም እምቢ የማለት መብት አለዎ።

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ፕሮግራምን ላለመቀበል ከመረጡ ከዚህ በታች ያሉትን ዝርዝር እያንዳንዳቸውን በጥንቃቄ ያንብቡ እና ይምረጡ ወይም ምልክት ያድርጉ። በመግለጫው ወይም ዐ/ነገሩ መጨረሻ ላይ ፊርማዎትን (initials) ያኑሩ። እንደዚያ ማድረግዎ እያንዳንዱን መግለጫ ወይም ዐ/ነገር መረዳትዎን እና መስማማትዎን ያመለክታል። እያንዳንዱን መግለጫ ወይም ዐ/ነገር ከፈረሙበት በኋላ ፈርመውና ቀን ጽፈውበት ቅጹን ለልጅዎ ት/ቤቱ እባክዎ ይመልሱ። ይህን ሠነድ ልጅዎ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ፕሮግራም በአሁኑ ጊዜ እንዳይሳተፍ አልቀበልም ማለትዎን ወይም አልፈልግም ማለትዎን ጠቅሰን በዶሴያችን ውስጥ የምናስቀምጠው ይሆናል።

- ☐ ስለልጄ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ፈተና/ምዘና እና ስለወቅቱ የትምህርት ለውጥ እውቀቱ አለኝ። ለተጨማሪ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት የተሰጠውን ምክር ተረድቻለሁ።
- ☐ ት/ቤቱ ለልጄ ስላቀረበው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ፕሮግራም ግንዛቤው አለኝ።
- ☐ ስለአለው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ትምህርታዊ ፕሮግራም ከት/ቤት ሠራተኛ ጋር የመወያየት እድሉ ነበረኝ።
- ☐ ት/ቤቱ የሰጠው ምክር ለልጄ ትምህርት በጣም ወሳኝ ነው ብሎ እንደሚያምን ተረድቻለሁ።
- ☐ የፌደራል ህጎችን በማክበር ረገድ፣ ልጄ "የእንግሊዝኛ ተማሪ" ለመሆን አሁንም ብቁ ሊሆን እንደሚችል እና በስቴቱ የእንግሊዝኛ ብየና መሠረት የስቴቱ የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ላይ በዓመት አድ ጊዜ በሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ፈተናን የንግሊዝኛ ተማሪ ማመቻቸቶች (accommodations) እንደሚያገኝ ተረድቻለሁ።

የህን አገልግሎትን ያለመቀበል የጽሑፍ መግለጫ በማንኛውም ጊዜ በማንኛውም ጊዜ መሻር እና ልጄ የቋንቋ መማር-ማስተማር ትምህርታዊ ፕሮግራም አገልግሎቶች እንዲሰጡት መጠየቅ እንደምችል ተረድቻለሁ።

**ይህ መረጃ በተሟላ ሁኔታ ወይም በደንብ በምረዳው ቋንቋ ቀርቦልኛል።**

**(በግልጽ የተጻፈ የወላጅ/አሳዳጊ ስም)**
___________________________________________

**የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ** **ቀን**
___________________________________________